የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፰
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No.68
ADDIS ABABA 24th September, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፯/፪ሺ፲፯

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ .................. ..ገጽ ፲፱ሺ፪፻፶

## Content

Proclamation No. 1387/2025

Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism (Amendment) Proclamation .................Page 19250

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፯/፪ሺ፲፯

**በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ ውስጥ ግልፅነት የጎደላቸውን ድንጋጌዎች ግልፅ በማድረግ ማሻሻል እና አዳዲስ ድንጋጌዎችን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለአተገባበር አመቺ የሆነ፣ ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን ያሟላ እንዲሁም ከሌሎች የሃገሪቱ ሕጎች ጋር የተጣጣመ እና ወቅታዊ ለሆኑ ችግሮች በቂ ምላሽ የሚሰጥ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፯/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1387/2025

**A PROCLAMATION TO AMEND THE PREVENTION AND SUPPRESSION OF MONEY LAUNDERING AND FINANCING OF TERRORISM PROCLAMATION**

**WHEREAS**, it is found necessary to clarify those unclear provisions and to include new provisions in the Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013;

**WHEREAS,** it is found necessary to incorporate provisions, which meets the international standards and is consistent with other laws of the country adequately responding to current problems;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism (Amendment) Proclamation No. 1387/2025."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ማሻሻያ

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተተክቷል፤

፬/ "አመንጭ ወንጀል" ማለት በዓይነት ሲገመት ወይም በጥሬ ገንዘብ ከአምስት መቶ ሺህ ብር በላይ የሚያመነጭ ማንኛውም ወንጀል ወይም የገንዘብ መጠኑ ከግምት ሳይገባ በአባሪ አንድ የተዘረዘሩ የወንጀል ዓይነቶችን ይጨምራል፡፡"

፪/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፭) ተተክቷል፤

፭/ "ንብረት" ወይም "ገንዘብ" ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ሀብት ሲሆን በሀብቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም መኖሩን የሚያረጋግጥ፣ የዲጂታል ወይም የኤሌክትሮኒክስ ዘዴን ጨምሮ በማንኛውም መልኩ የተገኘ፣ እና ሕጋዊ ሰነዶች ወይም መሣሪያዎች አካቶ እንደ ባንክ ክሬዲት፣ ትራቭለር ቼክ፣ የክፍያ ትዕዛዝ፣ አክሲዮን ወይም ቦንድ የመሰለ ማንኛውንም ሰነድ እና ከሀብቱ የተገኘን ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ገቢን ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን እንዲሁም ገንዘብን፣ ምርት ወይም አገልግሎትን ሊያስገኙ የሚችሉ ሌሎች ንብረቶችንም ይጨምራል፤"

፫/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፮) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተተክቷል፤

"ሐ) የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፮/፪ሺ፲፪ ላይ የተደነገገውን የሽብርተኝነት ድርጊት ትርጉምን ይጨምራል፤"

## 2. Amendment

Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013 is hereby amended as follows:

1/ The existing Sub-Article (4) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (4).

4/ "Predicate Offence" means any offence capable of generating more than 500,000 (Five Hundred Thousand) Birr in cash or in kind or crimes listed on the annex of this Proclamation regardless of the amount shall be considered as predicate offence.

2/ The existing Sub-Article (5) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (5).

5/ "property" or "Fund" means any assets, including, but not limited to, financial assets, economic resources, property of every kind, whether tangible or intangible, movable or immovable, however acquired, and legal documents or instruments in any form, including electronic or digital, evidencing title to, or interest in, such funds or other assets, including, but not limited to, bank credits, travelers cheques, bank cheques, money orders, shares, securities, bonds, drafts, or letters of credit, and any interest, dividends or other income on or value accruing from or generated by such funds or other assets, and any other assets which potentially may be used to obtain funds, goods or services.

3/ The existing Sub-Article (6) paragraph (C) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (6) paragraph (C

"C) Including the definition of terrorist act provided under Prevention and Suppression of Terrorism Crimes Proclamation No.1176/2020

፬/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፯) ፊደል ተራ (ሀ) ፤ (ለ) ፤ (ሐ) እና (መ) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተተክተዋል፤

"፯/ "ሽብርተኛ" ማለት በዚህ አዋጅ ወይም የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፮/፪ሺ፲፪ እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ፩ሺ፱፻፺፱ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል በወጣው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን አባሪዎች ላይ የተደነገገውን የሽብርተኝነት ድርጊት የፈፀመ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ነው፤"

፭/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፰) ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል፤

"ለ) የሽብር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፮/፪ሺ፲፪ ድንጋጌዎች መሠረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት ነው፤"

፮/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፱) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፱) ተተክቷል፤

"፱/ "የፋይናንስ ተቋም" ማለት ባንክ፣ የመድን ኩባንያ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ፣የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር፣ የውጭ ሀገር ባንክ እንደራሴ ቢሮ፣ የፖስታ የሐዋላ ተቋም፣ የሐዋላ ድርጅት፣ በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት፣ የውጭ ምንዛሬ አገልግሎት የሚሰጡ ቢሮዎች ወይም በብሄራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፤"

፯/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፳፩) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (፳፩) ተተክቷል፡፡

"፳፩/ "አገልግሎት" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺/፪ሺ፲፬ የተቋቋመው የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ነው፤"

4/ The existing Sub-Article (7) paragraph (a) (b) (c) and (d) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (7)

"7/ Terrorist" means any person, whether located in Ethiopia or elsewhere, who commits an offence listed under Prevention and Suppression of Terrorism Crimes Proclamation No.1176/2020 or as per this Proclamation, as well as in the annexse to the International Convention for Prevention and Suppression of Financing of Terrorism Crimes 1999.

5/ The existing Sub-Article (8) paragraph (b) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following paragraph (b)

"b) An organization so proscribed as terrorist in accordance with the provisions of the Anti-Terrorism Proclamation No. 1176/2012;

6/ The existing Sub-Article (9) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (9).

"9/ "Financial institution" means a bank, an insurance company, a micro finance institution, a capital goods finance company, a reinsurer, a micro finance provider, payment instrument issuer, payment system operator, a money transfer institution, representative office of a foreign bank, a postal money transfer institution, a digital financial service provider or such other similar institution as determined and licensed by the National Bank.

7/ The existing Sub-Article (21) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (21).

"21/"Service" means the Financial Intelligence Service established by the Council of Ministers Regulation NO 490/2022.

፰/ የአዋጁ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፳፪) በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፳፪) ተተክቷል፡፡

"፳፪/ "አግባብነት ያለው ባለሥልጣን" ማለት አገልግሎቱ፣ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አግልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ የፖሊስ ተቋም፣ የፍትሕ ሚኒስቴር ወይም የምርመራ ስራን በኃላፊነት የሚያከናውን አካል፣ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ አቻ የክልል ተቋማት ወይም የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ነው፤

፱/ የአዋጁ ነባር አንቀፅ ፫ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፫ ተተክቷል፤

"፫. ጥሬ ገንዘብና ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንበር አቋርጦ ስለማጓጓዝ

፩/ ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ የያዛቸውን ገንዘብ፣ ላምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን በተመለከተ አግባብ ባለው አካል በሚወጣው ሕግ መሠረት ለጉምሩክ ኮሚሽን የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

፪/ በፖስታ ወይም በካርጎ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጡ ጥሬ ገንዘብ፣ ላምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን ለጉምሩክ ኮሚሽን የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት የሚከናወን የማሳወቅ ሂደት ዓለም አቀፍ የንግድ ክፍያ ሥርዓቶችን እና የካፒታል እንቅስቃሴ በማያስተጓጉል መርህ የሚከናወን ይሆናል፡፡

፬/ ማንም ሰው ለጉምሩክ ኮሚሽን ገንዘብን፣ ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን አስመልክቶ ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ እንደሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት መግለጫ

8/ The existing Sub-Article (22) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (22).

"22/ "Competent Authority" means the Service, National Intelligence and Security Service, Information Network Security Administration, the police institution, Ministry of Justice, or other investigative body, Ministry of Revenue, Customs Authority, Ministry of trade and Regional Integration, any Regional Institutions who executes duties replacing the above institutions or any concerned regulatory authority.

9/ The existing Article 3 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 3.

"3. Cross-Border Transportation of Cash and Bearer Negotiable Instruments:

1/ Any person who enters or leaves the territory of Ethiopia in possession of currency, bearer negotiable instruments, precious stones or precious metals shall declare same to the Ethiopian Customs Authority as per the laws issued by the appropriate authority.

2/ Cash, bearer negotiable instruments, precious metals or stones that enters or leaves the territory of Ethiopia by mail or cargo shall be reported to the Ethiopian Customs Authority.

3/ The declaration process as per Sub-Article (1) and (2) of this Article shall not restrict international trade payment systems and capital movements.

4/ The Ethiopian Customs Authority shall have the power to request additional information on the source and the intended purpose and seize the currency, bearer negotiable instrument or precious metals or precious stones in case of a false

ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ ወይም ገንዘቡን፣ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮችን ወይም የከበሩ ብረቶችን በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል፣ በአመንጭ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ውጤት ስለመሆናቸው ወይም ወንጀሉን ለመፈፀሚያነት እንደሚውል ጥርጣሬ ሲኖር ኮሚሽኑ ምንጩን እና ለምን ዓላማ እንደሚውል ተጨማሪ መረጃ የመጠየቅ እና የመያዝ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፭/ በጉምሩክ አዋጅ የእቃ ውርስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት የተያዘ ገንዘብ፣ የክፍያ ሰነድን፣ የከበረ ብረትና የከበረ ድንጋይ በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፮/ የጉምሩክ ኮሚሽን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) ከተመለከተው ጥርጣሬ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለአገልግሎቱ ማቅረብ አለበት፡፡

፯/ የጉምሩክ ኮሚሽን ሕገ ወጥ ጥሬ ገንዘብን እና ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንበር አቋርጦ ከማጓጓዝ ጋር በተያያዘ እንዲሁም በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አግባብነት ካላቸው ባለሥልጣናት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

፰/ የጉምሩክ ኮሚሽን ጥሬ ገንዘብና ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንበር አቋርጦ ከማጓጓዝ ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን መረጃዎች አጠናቅሮ ይይዛል፦

ሀ) የገንዘብ መጠን፣ ላምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን እና የመግለጫ አቅራቢውን ማንነት የሚገልፅ መረጃን ያካተተ መግለጫዎች፣

ለ) ሀሰተኛ መግለጫዎች፣

ሐ. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ፣ በአመንጭ ወንጀል ወይም

disclosure or failure to disclose by any person as required under sub-Article (1) and (2) of this Article, or if there is suspicion of that all or parts of the currency, bearer negotiable instrument or precious metals or precious stones are proceeds or an instrumentality of money laundering, a predicate offence or financing of terrorism

5/ The provisions of the Customs Proclamation relating the forfeiture of goods shall be applicable with respect to currency, bearer negotiable instruments, precious metals, or precious stones seized under Sub-Article (4) of this Article.

6/ The Ethiopian Customs Authority shall submit to the Service any information relating to the existence of suspicion referred to in Sub-Article (4) of this Article.

7/ The Ethiopian Customs Authority shall work in cooperation with the competent authorities to prevent and suppress an illegal cross boarder cash, bearer negotiable instrument, money laundering and financing of terrorism.

8/ The Commission shall keep the information regarding cross boarder cash, bearer negotiable instrument:

a) All declarations, including the amount of currency, bearer negotiable instruments and identification of data of the reporter,

b) False declarations, and

c) Laundering of proceeds of crime, suspicious information related to a crime of origin or financing terrorism.

ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ጋር የተያያዙ የጥርጣሬ መረጃዎች፡፡

፲/ የአዋጁ አንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተተክቶ ከአዋጁ ነባር አንቀፅ ፭ ንዑስ አንቀፅ (፪) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፫)፣ (፬)፣ (፭)፣ (፮)፣ (፯) እና (፰) ተጨምረው እንደሚከተለው ተደንግገዋል።

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋሙ ወይም የተመዘገቡ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት፡-

ሀ) ስለ ተጠቃሚ ባለቤቶቻቸው እንዲሁም ስለ አመራርና የቁጥጥር አወቃቀራቸው በቂ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ መያዝ አለባቸው፤

ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተያዘውን መረጃ በጊዜው እንዲደርስ ማድረግን ጨምሮ ተጠቃሚ የሆነውን ባለቤት ለመወሰን አግባብነት ካላቸው ባለሥልጣናት ጋር በተቻለ መጠን መተባበር፤ እና

ሐ) የተጠቃሚ ባለቤትነት መረጃ ላይ በቂ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃን ለማቅረብ ከፋይናንስ ተቋማት እና ከተሰየሙ የገንዘብ ነክ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች እና የሙያ ዘርፎች ጋር መተባበር አለባቸው።

፫/ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና በክልል ደረጃ አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት ስለ ተጠቃሚ ባለቤትነት፡-

ሀ) የሚሰበሰቡና የሚያዙ መረጃዎችን ሌሎች ሥልጣን ያላቸው አካላት በጊዜው ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ፤

ለ) ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ በአስተማማኝ እና ገለልተኛ ምንጮች የተረጋገጠ ስለመሆኑ፤ እና

ሐ) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከፈረሰ በኋላ መረጃው ቢያንስ ለአሥር ዓመታት ያህል የሚቆይበትን ሁኔታ፤

ማረጋገጥ አለባቸው።

10/ The existing Sub-Article (1) of Article 5 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1), and new Sub-Article (3), (4), (5), (6), (7) and (8) are added next to the existing Sub-Article (2) of Article 5.

1/ Legal persons established or registered in Ethiopia shall:

a) Maintain adequate, accurate and up-to-date information on their beneficial owners, administration and control structure;

b) Co-operate with competent authorities to the fullest extent possible in determining the beneficial owner, including to avail information hold pursuant to Sub-Article (1) of this Article to competent authorities in a timely manner;

c) Co-operate with financial institutions, designated non-financial business and professions to provide adequate, accurate and up-to-date information on the company's beneficial ownership information.

3/ Competent Authorities, including the Ministry of Revenues, and Ministry of Trade and Regional Integration or their equivalent at the Regional State levels, shall ensure that beneficial ownership information is:-

a) Collected and maintained in a manner that allows timely access by the other competent authorities.

b) Verified through reliable and independent sources to ensure its accuracy; and

c) Maintained for at least ten years after the dissolution of the legal person.

፬/ አግባብነት ላላቸው ባለሥልጣናት፣ ለፋይናንስ ተቋማት፣ እና ለተሰየሙ የገንዘብ ነክ ያልሆኑ ንግዶች እና የሙያ ዘርፎች ተደራሽ የሆነ ተጠቃሚ የባለቤትነት ማዕከላዊ መዝገብ ቤት በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ይቋቋማል፣ይተዳደራል።

፭/ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት በሚቋቋሙበት ጊዜ የተጠቃሚ ባለቤትነት መረጃን ለማዕከላዊው መዝገብ ቤት ማሳወቅ እና በሂደት ማንኛውም ለውጥ በተደረገ ጊዜም ለውጡ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ፲፬ (አስራ አራት) ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው።

፮/ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት መሠረታዊ እና የተጠቃሚ ባለቤትነት መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ምርመራ እና ኦዲት የመስራት እንዲሁም ተገቢ የማስፈፀሚያ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን አላቸው።

፯/ የተጠቃሚ ባለቤትነት የሚመለከቱ የግልፅነት ግዴታዎችን ያለማክበር ሁኔታ ሲኖር የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የገንዘብ ቅጣቶችን እና በንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ገደቦችን ጨምሮ ማዕቀቦችን ሊጥል ይችላል።

፰/ የሚስጥራዊነት መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት የተጠቃሚ ባለቤትነት መረጃ ተደራሽነትን ለውጭ ሃገር ባለሥልጣናት ለማመቻቸት የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ የትብብር አሰራሮችን የማጠናከር ኃላፊነት አለባቸው።

፲፩/ ከአዋጁ አንቀፅ ፲፩ ንዑስ አንቀፅ (፪) ፊደል ተራ (ረ) ቀጥሎ አዲስ ፊደል ተራ (ሰ) ተጨምሯል፡፡

"ሰ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ (ለ) መሠረት የሚደራጅ ቡድን ውስጥ የሚመደቡ ሠራተኞች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ እና ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን በተመለከተ በቂ ሥልጠና የወሰዱ መሆን አለባቸው፤"

4/ A central beneficial ownership registry shall be established and maintained by the Ministry of Trade and Regional Integration ensuring access for competent authorities, financial institutions, and designated non-financial businesses and professions.

5/ Legal persons shall provide beneficial ownership information to the central registry at the time of incorporation and update it within 14 days of any change.

6/ The Ministry of Trade and Regional Integration, and other Relevant Competent Authorities shall have the power to conduct inspections and audits to verify compliance with basic and beneficial ownership requirements and take appropriate enforcement actions.

7/ The Ministry of Trade and Regional Integration may impose sanctions, including monetary penalties and restrictions on business activities, for failure to comply with beneficial ownership transparency obligations.

8/ Competent authorities shall strengthen international cooperation mechanisms to facilitate access to beneficial ownership information by foreign competent authorities, subject to confidentiality safeguards.

11/ The following new Sub-Article (2) paragraph (g) is added next to Sub-Article (2) paragraph (f) of Article 11.

g) Employees assigned to a team organized in accordance with Sub-Article (2) paragraph (b) of this Article shall have received adequate training in the field of money laundering and terrorist financing."

፲፪/ የአዋጁ አንቀፅ ፲፱ ንዑስ አንቀፅ (፫) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (፫) ተተክቶ፣ ከንዑስ አንቀፅ (፫) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፬) እና (፭) ተጨምረዋል።

፫/ አገልግሎቱ ከጉዳዩ ክብደት የተነሳ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አጠራጣሪ የሆነን ግብይት ከሰባት የስራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ እንዲታገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ድንጋጌ መሠረት በአገልግሎቱ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ፤ በፍርድ ቤት ውሳኔ ተጨማሪ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ካልሆነ በስተቀር፤ እግዱ በራሱ ቀሪ ይሆናል፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፫ ድንጋጌ መሠረት የደረሰውን የእግድ ትዕዛዝ ያለምንም መዘግየት የሕግ ማስከበር ኦፊሰሩ መፈፀም አለበት፡፡

፲፫/ ከአዋጁ አንቀፅ ፳፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሠ) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ (ረ) ተጨምሯል፤ ነባሩ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተተካ ሲሆን ከንዑስ አንቀፅ (፪) ቀጥሎ አዲስ ንዑሳን አንቀፆች (፫)፣ (፬)፣ (፭)፣ (፮)፣ (፯)፣ (፰)፣ (፱)፣ (፲)፣ (፲፩) እና (፲፪) ተጨምረው እንደሚከተለው ተደንግገዋል፡

ረ) በሽፋን ሥር ስለሚደረግ ምርመራና በቁጥጥር ሥር የሚደረግ ማስተላለፍ ለመጠቀም፤ የሚያስችል ትዕዛዝ ለወንጀል መርማሪ አካላት መስጠት ይችላሉ፡፡

፪/ የመርማሪ አካል በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ሥር የተደነገጉ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚችለው ፍርድ ቤት አስተማማኝ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ ሲፈቅድ ብቻ ነው።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም መርማሪ አካል አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመው በአካባቢው ያለውንና የሚመለከተውን የዓቃቤ ሕግ ተቋም የበላይ ኃላፊ በማስፈቀድ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስረጃ ሊሰበስብ ይችላል፡፡

12/ The existing Sub-Article (3) of Article 19 of the Proclamation is deleted and replaced by new Sub-Article (3), and after Sub-Article (3) new Sub-Articles (4) and (5) are added as the following.

3/ If, by reason of the seriousness of the case, the Service considers it necessary, it may order the suspension of a suspicious transaction for a period not to exceed seven working days.

4/ The period of suspension ordered by the Service in accordance with Sub-Article (3) of this Article will be expired unless further suspension is ordered by Court.

5/ The suspension order stipulated under Sub-Article (3) of this Article shall be executed by the Compliance Officer without delay.

13/ The following new paragraph (f) is added after Sub-Article (1) paragraph (e) of Article 25. Sub-Article (2) of Article 25 is deleted and replaced by new Sub-Article (2); after Sub-Article (2) new Sub-Articles (3), (4), (5), (6), (7), (8), (9), (10), (11) and (12) are added as follows.

f) Theycan issue orders to criminal invesigators to use under cover interrogation and custodlia interrogation.

2/ An Investigative body may use the evidence-gathering techniques provided in Sub-Article (1) of this Article only if the Court approves for the use of such techniques.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, in the event of emergency, the Investigative body may gather evidence with the permission of the head of the relevant prosecutor's office in the area.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት መርማሪ አካል ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስረጃ መሰብሰብ በጀመረ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ምክንያቶቹንና በዓቃቤ ሕግ የተሰጠውን ጊዜያዊ ፈቃድ ጨምሮ ለፍርድ ቤት በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ፍርድ ቤቱም የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል፡፡

፭/ ፍርድ ቤት የምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበስብ ለመርማሪ አካል ፈቃድ ሲሰጥ፡-

ሀ) ማስረጃ ስለሚሰበስብበት ዘዴ እና ስለሚከናወንበት አግባብ፤

ለ) የሚከናወንበት ጊዜ በተመለከተ ተገቢውን ትዕዛዝ፤ መስጠት አለበት፡፡

፮/ የማስረጃ ማሰባሰቢያው ዘዴ ጠለፋ ወይም ክትትል እንደሆነ ጠለፋው ወይም ክትትሉ የሚደረግበትን የስልክ፤ የፋክስ፤ የሬዲዮ፤ የኢንተርኔት፤ የኤሌክትሮኒክስ፤ የፖስታና የመሳሰሉትን የግንኙነት መስመሮች አድራሻ ወይም መለያ መጥቀስ አለበት፡፡

፯/ ማንኛውም የመገናኛ አገልግሎት አቅራቢ በመርማሪ አካል ጠለፋውን ለማካሄድ ሲጠየቅ ጠለፋው በፍርድ ቤት ወይም በዓቃቤ ሕግ የበላይ ኃላፊ የተፈቀደ መሆኑን በማረጋገጥ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

፰/ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር በሕግ አስከባሪ አካላት በጠለፋ የተገኘ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ በጠለፋ በተገኘበት መልክ በቀጥታ ካልቀረበ በቀር ዋጋ አይኖረውም፡፡

፱/ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀፅ መሠረት የምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስረጃ ለማሰባሰብ የሚፈቅደው ጊዜ ከ ፺ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡ መርማሪ አካል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ የሚፈለገውን ማስረጃ ያላገኘ እና የምርመራ ዘዴዎቹን መጠቀሙ ተጨማሪ ጊዜ አስፈላጊ ለመሆኑ በቂ ምክንያት ያለው ከሆነ ፍርድ ቤቱን ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ፍርድ

4/ Pursuant to Sub Article (3) of this Article, the Investigator shall submit to the Court in writing the reasons by including the temporary permission of the prosecutor within 48 hour. the Court may examine the application and accept or dismiss the request. the decision of the Court is not appealable.

5/ When the Court authorizes the Investigative body to gather evidence for the investigation the Court shall give order about:

a) How evidence is gathered and how it is done;

b) How long the investigation technique is allowed.

6/ Where the evidence gathering technic is interception or surveillance, it should mention addresses of telephone, fax, radio, internet, electronics, postal or others similar communication lines or identifications applied for the interception or surveillance.

7/ Any communication service provider shall cooperate when it is requested by the Police to conduct the interception by ensuring the availability of Courts or the Minister's Higher Official authorization order.

8/ Evidence obtained through interception by the investigator domestically or abroad will not be valid unless it is directly presented in the form obtained by interception.

9/ The special investigation authorization granted by the Court in accordance with this Article shall not exceed 90 days. Where the investigative body petitions the Court for an extension of the time, the Court may for good cause extend its authorization of using special investigation technique. The Court may give extension by investigating the performance of the investigator and evaluating the

ቤቱም መርማሪው ያከናወነውን ተግባር፣ የተፈቀደው ዘዴ እያስገኘ ያለውን ውጤት በማገናዘብ እና አስፈላጊ መሆኑን በመመርመር ፍርድ ቤቱ ለሰላሳ ቀናት ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፲/ በዚህ አንቀፅ መሠረት የምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚቀርብ ጥያቄ፣ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ፈቃድ፣ የምርመራ ዘዴዎች እና በምርመራ ዘዴው የተገኙ መረጃዎችና ማስረጃዎች የማሰባሰቡ ሁኔታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በፖሊስ፣ በዓቃቤ ሕግ፣ በፍርድ ቤት እና መረጃው በደረሳቸው ሌሎች አካላት በሚስጥር መያዝ አለበት፡፡ ማስረጃ ማሰባሰቡ ከተጠናቀቀ በኋላም ለጉዳዩ በማስረጃነት የሚያገለግሉ ካልሆነ በስተቀር በምርመራ ዘዴው የተገኙት መረጃዎች መወገድ አለባቸው፡፡

፲፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ እና ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና የአመንጭ ወንጀሉ ምርመራ በትይዩ ይከናወናል፡፡

፲፪/ የንብረቱ ባለቤት የንብረት ምርመራ እየተካሄደበት መሆኑን እንዳያውቅ መርማሪው ተገቢውን የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

፲፬/ የአዋጁ ነባር አንቀፅ ፳፱ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፳፱ ተተክቷል፡፡

፳፱. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ

፩/ ማንኛውም ሰው ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ፡-

ሀ) የንብረቱን ሕገ-ወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሸፈን ወይም አመንጭውን ወንጀል የፈፀመው ሰው ከሕግ ተጠያቂነት እንዲያመልጥ ለማድረግ ንብረቱን የለወጠ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤

ለ) ንብረቱን፣ የንብረቱን ትክክለኛነት፣ ምንጩን፣ ቦታውን፣ ዝውውሩን ወይም የባለቤትነት መብትን የደበቀ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ እንደሆነ፤

significance of using special investigation technique for thirty additional days.

10/ In accordance with this Article, petition of special investigation technique, the authorization granted by the Court, evidences and information obtained through special investigation shall be kept in secret by Police, Public Prosecutor, Court and other organs which have obtained the information until the conditions completed. Where the evidence collected through the special investigation technique is not relevant as evidence, it shall be destroyed.

11/ The Predicate offence and the money laundering offence shall be investigated in parallel.

12/ The investigator must take appropriate precautions to ensure that the property owner does not know that the property is under investigation.

14/ The existing Article 29 is deleted and replaced by the following new Article 29;

29. Money Laundering

1/ Any person who knows that a property is the proceeds of a crime and who:

a) Converts or transfers the property for the purpose of concealing or disguising the illicit origin of the property or of assisting any person who is involved in the commission of the predicate offence to evade the legal consequences of his actions;

b) Conceals or disguises the true nature, source, location, disposition, movement or ownership of or rights with respect to the property;

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ከአመንጭ ወንጀል ፈፃሚው ውጭ የሆነ ሦስተኛ ወገን ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ የተረከበ ፣ በይዞታው ያደረገ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፤

፫/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የተጠቀሱትን ወንጀል የሚፈፅምን ሰው ለመርዳት ያደመ፣ የሞከረ፣ የደገፈ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈፀም ያማከረ እንደሆነ፤

በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ፲ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፭፻ሺ (አምስት መቶ ሺ) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪) እና (፫) ላይ የተዘረዘሩትን ድርጊቶች በቸልተኝነት የፈፀመ እንደሆነ የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ፭ ዓመት እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሺ) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪) እና (፫) መሠረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ፲፭ ዓመት እስከ ፳፭ ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን) ብር መቀጮ ሊደርስ ይችላል፡-

ሀ) የተፈፀመው አመንጭ ወንጀል በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪) እና (፫) ከተመለከተው በላይ የእስር ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ፤

ለ) ወንጀሉ የተፈፀመው በንግድ ወይም በስራ ተግባርነት ተይዞ ከሆነ፤

ሐ) የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከዓላማዎቹ አንዱ አድርጎ የፈፀመው ከሆነ፤

2/ without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, any third party who knows that a property is the proceeds of a crime acquires, possesses or uses the property;

3/ Participates in the commission, conspires to commit, attempts to commit or aids, abets, facilitates or counsels the commission of any of the elements of the offence mentioned in Sub-Articles (1) and (2) of this Article;

Commits an offence and shall, without prejudice to the confiscation of the property, be punishable with rigorous imprisonment from ten years up to fifteen years and with fine not exceeding Birr 500,000 (Five Hundred Thousand).

4/ Any person who commits the elements of the offence mentioned in Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article negligently shall, without prejudice to the confiscation of the property, be punishable with rigorous imprisonment from five years up to ten years and with fine not exceeding Birr 200,000 (Two Hundred Thousand).

5/ The penalties imposed under Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article shall be increased to rigorous imprisonment from fifteen years up to twenty-five years and with fine not exceeding Birr 1,000,000 (One Million):

a) If the predicate offence carries a penalty of imprisonment exceeding that specified in Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article;

b) If the offence is perpetrated in the pursuit of a trade or occupation;

c) If the offence is perpetrated as part of the activities of an organized criminal group;

መ) ሕጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ግምት ብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊየን) ወይም የሚበልጥ ከሆነ፣ ወይም

ሠ) ወንጀሉ የተፈፀመው ሌላ ወንጀል እንዲሰራ ለማመቻቸት ከሆነ፡፡

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ (፩)፣ (፪) እና (፫) ላይ የተዘረዘሩትን ድርጊቶች በቸልተኝነት ሲፈፀሙ ከላይ በንዑስ አንቀፅ (፭) ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች በመክበድ ከ፲ ዓመት እስከ ፲፭ ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ፭፻ ሺህ (አምስት መቶ ሺህ) ብር መቀጮ ሊደርስ ይችላል፡፡

፯/ ለዚህ አንቀፅ ድንጋጌ አፈፃፀም ሲባል፡-

ሀ) የተከሳሽ የሀሳብ ክፍል ወይም ወንጀሉን ለመፈፀም የተነሳበት ዓላማ ከተጨባጭ የሁኔታዎች ክስተት በመነሳት ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፣

ለ) የንብረቱ ምንጭ ሕገ-ወጥ መሆኑን ለማስረዳት በተከሳሽ ላይ በአመንጭው ወንጀል የጥፋተኝነት ፍርድ መሰጠቱ የግድ የሚያስፈልግ አይሆንም፣

ሐ) የአመንጪው ወንጀል ድርጊት ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የተፈፀመ ቢሆንም ድርጊቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢፈፀም ኖሮ ወንጀል ሆኖ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ የመነሻው ወንጀል ይህንኑ ድርጊት ጭምር የሚያካትት ይሆናል፣

መ) በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል ወንጀል ለመፈፀም መሞከር፣ መደገፍ፣ ማመቻቸት ወይም ማማከር ወንጀሉ እንደተፈፀመ ተቆጥሮ በተመሳሳይ የሚያስቀጣ ይሆናል፣

ሠ) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል ተጠያቂነት አመንጪውን ወንጀል የፈፀመውን ሰውም የሚመለከት ይሆናል።

d) If the amount of fund or property laundered is more than Birr 20,000,000 (Twenty Million);

e) If the purpose is promoting the carrying on of further criminal activity.

6/ If the elements of the offence mentioned in Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article are committed negligently, the penalty may be increased from 10 years to 15 years of imprisonment and a fine of up to Birr 500,000 (Five Hundred Thousand) on the grounds listed under Sub-Article (5) above.

7/ In applying the provisions of Sub-Article (1) of this Article:

a) Knowledge, intent, or purpose as constituent elements of the offence may be inferred from objective factual circumstances;

b) It may not be required to obtain the conviction of the predicate offence to prove the illicit origin of the property;

c) The predicate offence also includes actions committed outside of the national territory, if they would have constituted offences if they had been committed within the territory of Ethiopia;

d) Attempting, aiding, abetting, facilitating or counseling the commission of money laundering shall be punishable equally as if the offence had been completed;

e) Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the offence of money laundering shall also apply to persons who have committed the predicate offence.

፲፭/ የአዋጁ አንቀፅ ፴ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ)፣ (ሐ) እና (ቸ) ተሰርዘው በአዲስ ንዑሳን አንቀፆች (፩) (ሀ)፣ (ሐ) እና (ቸ) ተተክተው፣ በአዋጁ አንቀፅ ፴ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ የነበረው የቅጣት መጠንም ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተደንግገዋል፡-

ሀ) ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የያዘውን ጥሬ ገንዘብ ወይም ለአምጭው የሚከፈሉ የገንዘብ ሰነዶችን ያልገለፀ ወይም የሀሰት ማስረጃ የሰጠ ወይም በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ ለማሳወቅ ፈቃደኛ ካልሆነ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ በተደነገገው መሠረት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውን አካላት ተጠቃሚ የሆኑ ባለቤቶቻቸውን እና የአመራር መዋቅራቸውን የሚመለከት የተሟላ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች ያልያዘ እንደሆነ፤

ቸ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳ እና ፳፫ የተደነገገውን በመተላለፍ መረጃ ለደንበኛ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ሰው አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር ፩፻ ሺህ (አንድ መቶ ሺህ) እስከ ፭፻ ሺህ (አምስት መቶ ሺህ) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፲፮/ በአዋጁ አንቀፅ ፴፩ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ) ስር ከፍፁም ንዑስ አንቀፅ (፫) ቀጥሎ አዲስ ፍፁም ንዑስ አንቀፅ (፬) ተጨምሮ፤ የአዋጁ ነባር አንቀፅ ፴፩ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የቅጣት መጠን ተሻሽሎ፣ እንዲሁም ከንዑስ አንቀፅ (፫) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተጨምሮ እንደሚከተለው ተደንግገዋል፡-

(፬) የሽብርተኝነት ድርጊቶችን ለመፈፀም፣ ለማቀድ ወይም ለማዘጋጀት ወይም ለመሳተፍ ወይም ከሽብርተኝነት ጋር የተገናኘ ሥልጠና ለመስጠት ወይም ለመሰልጠን ከሚኖርበት ወይም ዜጋ ከሆነበት ሀገር ውጭ ወደ ሌላ ሀገር የሚጓዙ ግለሰቦችን ለመደገፍ፤

15/ The existing paragraphs (A), (C) and (l) of Sub-Article (1) of Article 30 of the Proclamation is deleted and replaced by new Paragraph (A), (C) and (l) of Sub-Article (1) of Article 30; and the penalty is amended as the following:

a) Fails to declare or gives false declaration or refused to declare of Cash or Bearer Negotiable Instruments to the Ethiopian Revenue and Customs Authority, when entering or leaving Ethiopia;

c) Fails to maintain adequate, accurate and current information on the beneficial ownership and control structure of legal persons as required pursuant to Article 5 of this Proclamation;

i) discloses information to a customer or a third party in contravention of Article 20 and 23 of this Proclamation;

Commits an offence and shall be punished with imprisonment from three to five years and a fine of Birr 100,000 (One Hundred Thousand) up to 500,000 (Five Hundred Thousand).

16/ Following paragraph (A) (3) of Sub-Article (1) of Article 31 of the Proclamation new paragraph (A) (4) of Sub-Article (1) is added; the penalty provided in Sub-Article (1) and (2) of Article 31 is amended; and after the existing Sub-Article (3) of Article 31 the following new Sub-Article (4) is also added:

(4) To finance the travel of individuals who travel to a State other than their States of residence or nationality for the purpose of the perpetration, planning, or preparation of, or participation in, terrorist acts or the providing or receiving of terrorist training;

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፭፻ ሺህ (አምስት መቶ ሺህ) የማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ፲፭ ዓመት እስከ ፳፭ ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ብር ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን) መቀጮ ሊደርስ ይችላል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀፅ ድንጋጌ አፈፃፀም ሲባል የተከሳሽ የሀሳብ ክፍል ወይም ወንጀሉን ለመፈፀም የተነሳበት ዓላማ ከተጨባጭ የሁኔታዎች ክስተት በመነሳት ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፡፡

፲፯/ የአዋጁ አንቀፅ ፴፪ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሰርዞ እና ንዑስ አንቀፅ (፪) ወደ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሸጋሽጎ የቅጣት መጠኑ ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተደንግጓል፡-

፩/ ለዚህ አዋጅ ዓላማ፡-

ሀ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ወይም በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ከተሰጠ ትዕዛዝ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ምርመራ ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ወይም ቁስ ወደ ሀሰት የለወጠ፣ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ያስወገደ ወይም ወደ ሀሰት ሰነድነት እንዲለወጥ፣ እንዲጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዲወገድ የፈቀደ እንደሆነ፤

ለ) በአገልግሎቱ ዘንድ የተቀመጠውን መረጃ ሆን ብሎ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሚፈለገው ዓላማ እንዳይውል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት

Whoever is found guilty of a crime under this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment for a term not exceeding 10 to 15 years and a fine not exceeding 500,000 (Five Hundred Thousand) Birr, without prejudice to the confiscation of his property.

2/ The penalties imposed under Sub-Article (1) of this Article may be increased to rigorous imprisonment from 15 to 25 years and with fine not exceeding Birr 1,000,000 (One Million);

4/ In applying the provisions of this Article knowledge, intent, or purpose as constituent elements of the offence may be inferred from objective factual circumstances.

17/ The existing Sub-Article (1) of Article 32 of the Proclamation is deleted, Sub-Article 2 is renumbered as Sub-Article (1) and the penalty is amended as follows:

1/ For the purpose of this proclamation:

a) any person falsifies, conceals, destroys or otherwise disposes of or causes or allows the falsification, concealment, destruction or disposal of any document or material which is or is likely to be relevant to an investigation of money laundering or financing of terrorism or is subject to any order made in accordance with the provisions of this Proclamation;

b) intentionally destroys the information stored by the Service or in any other way prevents it from being used for the intended purpose;

c) induces or threatens a person who is or can be a witness for an act of money laundering or financing of terrorism or uses violence against

ድርጊት ላይ ምስክር የሆነን ወይም ለመሆን የሚችል ሰውን እንዳይመሰክር የደለለ ወይም ያስፈራራ ወይም በምስክሩ ወይም ከምስክሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የኃይል ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፤

ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፶ ሺ. (ሀምሳ ሺ.ህ) እስከ ፩፻ ሺ. (አንድ መቶ ሺ.ህ) በሚደርሰ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፲፰/ ከአዋጁ አንቀፅ ፴፰ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑሳን አንቀፆች (፫) እና (፬) ተጨምረዋል፡፡

“፫/ አግባብነት ያለው ባለሥልጣን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶችን በሚመለከት መሠረታዊ ተጠቃሚ ስለሆኑ ባለቤቶቻቸው መረጃዎች ወይም ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶቻቸው ከሀገር ውጪ የሚገኙበትን አድራሻ በሚመለከት የጋራ የሕግ ድጋፍ ትብብር ሲልኩም ሆነ ሲቀበሉ የተቀበሉትን ምላሽ ጥራት መቆጣጠር አለባቸው፡፡

፬/ የፍትሕ ሚኒስቴር ለዚህ አዋጅ ዓላማ ሲባል የዓለም ዓቀፍ ትብብር ማዕከላዊ ባለሥልጣን ነው።

፲፱/ ከአዋጁ አንቀፅ ፶፩ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀፅ ቁጥር ፶፪ ተጨምሮ፤ የአዋጁ ነባር አንቀፆች ፶፪፣ ፶፫፣ ፶፬፣ ፶፭፣ ፶፮፣ ፶፯ እና ፶፰ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀፅ ፶፫፣ ፶፬፣ ፶፭፣ ፶፮፣ ፶፯ ፤ ፶፰ እና ፶፱ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

**፶፪. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፰ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎትን፣ የሕግ አስከባሪ ተቋማትን እና ተቆጣጣሪ አካላትን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀልን፣ አመንጪ ወንጀልን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ፤ እንዲሁም የፍትሕ ሚኒስቴር የሚመለከተው

the witness or a person who has close relationship with the witness to prevent the witness from testifying;

Commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from five to ten years and fine from Birr 50,000 to Birr 100,000.

18/ The following new Sub-Articles (3) and (4) are added after Sub-Article (1) and (2) of Article 38 of the Proclamation as follows;

3/ The competent authorities shall monitor the quality of the responses received when sending or receiving basic information about the beneficiary owners or addresses of the beneficiary owners abroad in relation to legal persons.

4/ For the purpose of this Proclamation, the Ministry of Justice shall be the Central Authority on international cooperation.

19/ The following new Article 52 is added after the existing Article 51 of the Proclamation; and the existing Articles 52, 53, 54, 55, 56, 57, and 58 of the Proclamation are re-numbered as 53, 54, 55, 56, 57, 58 and 59 respectively.

**52. Other Forms of International Cooperation**

1/ Notwithstanding with the provision of Article 38 (4) of this Proclamation, competent authorities, including the Financial Intelligence Service, law enforcement agencies, supervisory bodies and only the relevant unit of the Ministry of Justice for asset recovery over the same matter, shall provide the widest possible range of international cooperation in relation to money

የሥራ ክፍል ንብረት የማስመለስ ሂደት ላይ በተቻለ መጠን ከአቻና አቻ ካልሆኑ ሌሎች ተቋማት ጋር መጠነ ሰፊ መደበኛ ያልሆነ ዓለም አቀፍ ትብብር ማከናወን አለባቸው።

፪/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት ከአቻ እና አቻ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ትብብርን እና የመረጃ ልውውጥን ለማጠናከር የሁለትዮሽ ወይም የባለ-ብዙ ወገኖች ስምምነቶችን ማድረግ ይችላሉ።

፫/ አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት የፋይናንስ መረጃን፣ ምርመራን እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች መስጠትን ጨምሮ ከውጭ አቻ ተቋማት ለሚቀርቡት መደበኛ ያልሆነ የትብብር ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት አለባቸው።

፬/ በዚህ አንቀፅ ሥር ያሉ ዓለም አቀፍ የትብብር ጥያቄዎች ወቅታዊ፣ ቀልጣፋ እና ሚስጥራዊ በሆነ መንገድ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ግልፅ አሠራሮች በመያዝ መስተናገድ አለባቸው።

፭/ አገልግሎቱ ከውጭ የፋይናንስ መረጃ ክፍሎች እና አቻ ተቋማት ጋር ድንገተኛ የመረጃ ልውውጥ የሚከናወንባቸው ዘዴዎችን መዘርጋት አለበት።

፮/ አግባብነት ያላቸው ባለሥልጣናት ከፋይናንስ ተቋማት ወይም ከገንዘብ ነክ ያልሆኑ ንግዶች እና ሙያዎች የተመለከቱ የሚስጥራዊነት ሕጎችን ብቻ መሠረት በማድረግ የዓለም አቀፍ ትብብር ጥያቄዎችን ውድቅ ማድረግ የለባቸውም።

፯/ ዓለም አቀፍ ትብብርን መሠረት በማድረግ የሚገኝ መረጃ ለታለመለት ዓላማ ብቻ የሚውል፣ ሚስጥራዊነቱ የሚጠበቅ እና የመረጃ ጥበቃ ከለላ የሚደረግለት መሆን አለበት።

፳/ የአዋጁ አንቀፅ ፶፯ (በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፲፱) እንደተሸጋሸገው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፶፯ ተተክቷል፡፡

laundering, predicate offences, and terrorist financing to their counter and non-counterpart foreign bodies.

2/Competent Authorities may enter into bilateral or multilateral agreements to enhance cooperation and exchange of information with their counter and non-counter parts as may be necessary.

3/Competent Authorities shall rapidly respond to requests for assistance from foreign counterparts, including providing financial intelligence, investigative assistance, and other relevant information.

4/International cooperation requests under this Article shall be handled in a timely, efficient, and confidential manner, with clear procedures for prioritization.

5/The Financial Intelligence Service shall establish mechanisms for spontaneous exchange of information with foreign Financial Intelligence Units and counterpart agencies.

6/Competent authorities shall not refuse requests for international cooperation solely on the basis of secrecy laws related to financial institutions or designated non-financial businesses and professions.

7/ Information received through international cooperation shall be used only for the intended purpose and shall be subject to confidentiality and data protection safeguards.

20/ Article 57 of the Proclamation (as renumbered under Sub-Article (19) of this Article) is deleted and replaced as follows.

**፶፯. የዳኝነት ሥልጣን**

፩/ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል ክስ ከአመንጪ ወንጀል ጋር በተደራራቢነት ወይም ራሱን ችሎ ሲቀርብ የአመንጭ ወንጀሉን የመዳኘት ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀልንም የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀል ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አፅቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**57. Jurisdiction**

1/ The Court that has jurisdiction over predicate offences also has a jurisdiction over money laundering, where the money laundering charge is brought as a standalone or concurrent offence.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Federal High Court shall have first instance jurisdiction over the financing of terrorism.

**3. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 24th day of September, 2025**

**TAYE ATSIKE-SILASIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**